በጉምሩክ ኮሚሽን
የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
CUSTOMS COMMISSION
ADDIS ABABA KALITI CUSTOMS BRANCH OFFICE
የሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት የውስጥ ማስታወሻ

ቁጥር፡ ስ/አ/ጽ/ቤት 39/12
ቀን፡ 16/01/2012 ዓ.ም

ለ፦ ወጪና ንግድ ያልሆኑ ገቢ ዕቃዎች አወጣጥ የስራ ሂደት
ለ፦ ንግድ ገቢ ዕቃዎች አወጣጥ የስራ ሂደት
ለ፦ ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ የጉ/ሥ/ሥ/ አ/የስራ ሂደት
ለ፦ ኢስተርን ኢንዱስትሪ ፓርክ የጉ/ሥ/ሥ/ አ/የስራ ሂደት

ከ፦ ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
አ.አ. ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ጉዳዩ፦ የግብርና መካናይዜሽን መሣሪያዎች ይመለከታል፤

የጉምሩክ ኮሚሽን ኦፐሬሽን ዘርፍ በቁጥር 6/005/12 በቀን 14/01/2012 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ የገንዘብ ሚኒስቴር የግብርና ሜካናይዜሽን ማሽነሪዎች ዝርዝር ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው እንዲገቡ በቁጥር ማኢ.30/6/7 በቀን 12/01/2012 ዓ.ም ያሳወቀው መሆኑን አሳውቆናል፡፡

ስለሆነም ከመስከረም 12/01/2012 ዓ.ም ጀምሮ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በላከው አሰራር መሰረት ተገቢውን የጉ/ሥ/ሥርዓት በመፈጸም አገልግሎት እንዲሰጥ እያሳሰብኩ ለአፈጻጸም ይረዳችሁ ዘንድ 5 ገጽ ኮፒ ደብዳቤዎችን አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ

ለ፦ ም/ስራ አስኪያጅ (አምራች ወጪና ሌሎች ጣቢያዎች)
ለ፦ ም/ስራ አስኪያጅ (የንግድ ገቢ ዕቃዎች ኦፕሬሽን)
ለ፦ ም/ስራ አስኪያጅ (ህግ ተገዥነት)
አ.አ. ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

568
ን/ር.

ቃለ:

# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጉምሩክ ኮሚሽን

# THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA CUSTOMS COMMISSION

ቀን 14 መስከረም 2012
Date
ቁጥር 6/005/12
Ref.No.

የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ፅ/ቤቶች በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የግብርና መካናይዜሽን መሳሪያዎች ይመለከታል</u>

የግብርና ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት ግንቦት 22 ቀን 2009 ዓ/ም ባካሄደው ስብሰባ አገራዊ የምግብ ሥርዓት ዕድገት እና የምግብ ዋስትናን በቤተሰብ ደረጃ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን በበቂ ሁኔታ ለአርሶ አደሩ ለማቅረብ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ የሚፈልጉ የግብርና መካናይዜሽን መሳሪያ ዓይነቶችን ታሕሳስ 22 ቀን 2011 ዓ/ም በቁጥር 13/36/9/176 የግብርና ሚኒስቴር በፃፈው ደብዳቤ መነሻነት የገንዘብ ሚኒስቴር የግብርና ሜካናይዜሽን ማሽነሪዎች ዝርዝር ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ በደብዳቤ ቁጥር ማሒ30/6/7 ቀን 12 መስከረም 2012 ዓ/ም ለኮሚሽናችን አሳውቆናል፡፡

ስለሆነም ከመስከረም 12 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በላከው አሰራር መሰረት አስፈላጊውን የጉምሩክ ስነ ስርዓት በመፈፀም መስተንግዶ እንዲሰጥ እየገለፅን ለአፈፃፀም ይረዳችሁ ዘንድ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የላከልንን ደብዳቤ አራት /4/ ገፅ ኮፒ አባሪ አያይዘን የለክን መሆኑን እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ዮናስ ተ/ወልድ
የጉምሩክ ኦፐሬሽን ዘርፍ
ም/ኮሚሽነር (ተወካይ)

<u>ግልባጭ</u>

- ለጉምሩክ ኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለታሪፍ ምደባና የስሪት አገር አወሳሰን ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት

<u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>

ለዘመናዊና ፍትሀዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

☎ +251 116 62 98 00
+251 116 62 98 19
✉ 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

7878
3/01/12

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር
Ref.No. ማ7230/6/12
ቀን
Date 12/1/2012

ለገቢዎች ሚኒስቴር
ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

የግብርና ትራንስፎርሜሽን ምክር ቤት ግንቦት 22 ቀን 2009 ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ አገራዊ የምግብ ሥርዓት ዕድገት እና የምግብ ዋስትናን በቤተሰብ ደረጃ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን በበቂ ሁኔታ ለአርሶ አደሩ ለማቅረብ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ የሚፈለጉ የግብርና ሜካናይዜሽን መሣሪያ ዓይነቶችን ታህሳስ 22 ቀን 2011 ዓ.ም በቁጥር 13/36/9/176 የግብርና ሚኒስቴር በተጻፈው ደብዳቤ መነሻነት ከመ/ቤታችን ሚያዚያ 28 ቀን 2011 ዓ.ም በቁጥር ማኢ-30/7/351 በተጻፈ ደብዳቤ የግብርና ሜካናይዜሽን ማሽነሪዎች እና የመስኖ ቴክኖሎጂ መሣሪያዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ መፈቀዱ ታወሳል፡፡ ይሁንና እነዚህ የተፈቀዱት እቃዎች ለጉምሩክ አፈጻጸም አስቸጋሪ በመሆናቸውና ለቁጥጥር አመቺ ባለመሆናቸው እንዲሁም በገቢ አሰባሰቡ ላይ አሉታዊ ውጤት ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ጉዳዩ በድጋሚ ታይቶ ውሳኔ እስከሚሰጥበት ድረስ የተላለፈው ማሻሻያ ለጊዜው ተግባራዊ ሳይደረግ እንደሚቆይ ግንቦት 06 ቀን 2011 ዓ.ም በቁጥር 6.163/11 ከጉምሩክ ኮሚሽን በተጻፈ ደብዳቤ መገለጹ ይታወሳል፡፡

ይህን ተከትሎም እነዚህ የግብርና መካናይዜሽን መሣሪያዎች ሲፈቀዱ ታክሱን በሚያስተዳድረው መ/ቤት ላይ በአፈጻጸም ረገድ ችግር እንዳያስከትሉ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላትና ከግሉ ዘርፍ ጋራ በተለያዩ ጊዜያት ውይይት የተደረገ ሲሆን፣ በውይይቱም የእነዚህ እቃዎች አፈቃቀድ በጉምሩክ አፈጻጸምም ሆነ በታክስ አሰባሰቡ ላይ ችግር በማያስከትልበት መልኩ እንዲሆን ከመግባባት ተደርሷል፡፡

በዚህም ከታች በሠንጠረዡ የቀረቡት የግብርና ሜካናይዜሽን ማሽነሪዎች ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ ተወስኗል፡፡



ስልክ Tel 251-11-155 24 00,22 66 98 / 251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ. P.O.Box 1905,1037 / እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ Fax 251-11-156 01 24,55 14 96 / 251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa-Ethiopia

ቁጥር
Ref.No.
ቀን
Date

| ተ.ቁ | የታሪፍ ቁጥር | የእቃው ዓይነት |
|---|---|---|
| 1 | 8424.4100 | ተንቀሳቃሽ ስፕሬየሮች |
| 2 | 8424.4900 | በራሳቸው የሚሰሩ መርጫዎች (Self propelled sprayers) |
| 3 | 8424.8200 | አግሪካልቸራል ወይም ሆርቲካልቸራል መርጫ መሣሪያዎች |
| 4 | 8424.8900 | ለሆርቲካልቸር ወይም አግሪካልቸር የሚሆኑ በልዩ ዲዛይን የተደረጉ መርጫዎች |
| 5 | 8432.3100 | የኖቲል ቀጥተኛ ሲደሮች፣ ፕላንተሮች እና ትራንስፕላንተሮች |
| 6 | 8432.4100 | ፍግ መበተኛዎች |
| 7 | 8432.4200 | ማዳበሪያ ማሰራጫዎች |
| 8 | 8433.2000 | ማጨጃዎች፣ ትራክተር ላይ የሚገጠሙ ካተር ባር ጭምር |
| 9 | 8433.3000 | ድርቆሽ ማዘጋጃ መሣሪያዎች |
| 10 | 8433.4000 | የገለባ ወይም የመኖ ማሰሪያ ማሽኖች፣ ፒክ አፕ ማሰሪያዎች ጭምር |
| 11 | 8433.5100 | ማጨጃና መውቂያ በአንድነት የያዙ ማሽነሪዎች |
| 12 | 8433.5200 | የመውቂያ ማሽነሪዎች |
| 13 | 8433.5900 | በትራክተር ላይ ሚገጠም የጥጥና የሌሎች ሰብሎች ምርት መሰብሰቢያ |
| 14 | 8701.1013 | ባለ አንድ አክሰል ትራክተሮች |
| 15 | 8701.2013 | የሲሚትሬለር መጎተቻ ትራክተሮች |
| 16 | 8701.3013 | የእርሻ ትራክተር |
| 17 | 8701.9113 | የኢንጅን ጉልበታቸው ከ18 ኪሎ ዋት ያልበለጠ ትራክተሮች |
| 18 | 8701.9213 | የኢንጅን ጉልበታቸው ከ18 ኪሎ ዋት የበለጠ ነገር ግን ከ37 ኪሎ ዋት ያልበለጠ ትራክተሮች |
| 19 | 8701.9313 | የኢንጅን ጉልበታቸው ከ37 ኪሎ ዋት የበለጠ ነገር ግን ከ75 ኪሎ ዋት ያልበለጠ ትራክተሮች |



ስልክ Tel 251-11-155 24 00,22 65 98 251-11-155 00 81,83 86 89
ፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037 እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ Fax 251-11-156 01 24,55 14 96 251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa-Ethiopia

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር
Ref.No.________________
ቀን
Date ________________

| ተ.ቁ | የታሪፍ ቁጥር | የእቃው ዓይነት |
|---|---|---|
| 20 | 8701.9413 | የኢንጅን ጉልበታቸው ከ75 ኪ.ሎ ዋት የበለጠ ነገር ግን ከ130 ኪ.ሎ ዋት ያልበለጠ ትራክተሮች |
| 21 | 8701.9513 | የኢንጅን ጉልበታቸው ከ130 ኪ.ሎ ዋት የበለጠ ትራክተሮች |

ከዚህ ጋር በተያያዘ ግብርና ሚኒስቴር:-

1. ትራክተር በአገር ውስጥ ተከማችቶ የሚገኝ እና በአገር ውስጥ በመመረት ላይ ቢሆንም የግብርናውን ፍላጎት አያሟላም። ስለዚህ በአገር ውስጥ ተከማችቶ የሚገኘውንና የሚመረተውን አቅም እስከመጨረሻው መጠቀምና ቅድሚያ ለሀገር ውስጥ አቅራቢዎች በመስጠት ከዚህ ውጪ ያለውን የገበያ ጉድለት ከውጭ እንዲመጣ በማድረግ፣ ነገር ግን አገር ውስጥ ተመርተው የሚገኙትና የሚመረቱትን ቅድሚያ በመስጠት ጥቅም ላይ ማዋል የማይቻል ከሆነ ምክንያቶቹን ለገንዘብ ሚኒስቴር በዝርዝር እንዲያቀርብ፣

2. እቃዎቹ ለታለመለት ዓላማ መዋላቸውን ግብርና ሚኒስቴር ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርግ አፈጻጸሙንም በየስድስት ወሩ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት እንዲያቀርብ፣

3. እቃዎቹ ለአርሶ/አርብቶ አደሩ ወይም ለተጠቃሚው ሲደርሱ የተሸጡበትን ዋጋ ሪፖርት በየሦስት ወሩ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት እንዲያቀርብ፣

4. ይህ የቀረጥና ታክስ ማበረታቻ በግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ላይ ያስከተለውን ውጤት (Impact Assesement) በጥናት በየዓመቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት እንዲያቀርብ፣

እናሳስባለን።



ስልክ Tel 251-11-155 24 00,22 65 98 / 251-11-155 ... 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O Box 1905,1037 አፀፉን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ Fax 251-11-156 01 24,55 14 96 / 251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa-Ethiopia

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር
Ref.No. ____________________

ቀን
Date ____________________

ስለዚህ የተደረገው ማሻሻያ ከመስከረም 12 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ኢዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ፡-

- ለግብርና ሚኒስቴር
  አዲስ አበባ
- ለታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
  ገንዘብ ሚኒስቴር



ስልክ Tel 251-11-155 24 00,22 66 98 / 251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲሰጡን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ Fax 251-11-156 01 24,55 14 96 / 251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa-Ethiopia